# በውጭ ሀገር በሥራ የሚሰማሩ ዜጎችን የመድን ሽፋን ለመወሰን የወጣ መመሪያ

ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር

አዲስ አበባ

የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር
ሪከርድና ማህደር
Record and File
Ministry of Labour and Social Affairs

# በውጭ ሀገር በሥራ የሚሰማሩ ዜጎችን የመድን ሽፋን ለመወሰን የወጣ መመሪያ

## 1. የመመሪያው አስፈላጊነት

ይህን መመሪያ ማውጣት ያስፈለገበት ምክንያት በአዋጅ ቁጥር 923/2008 አንቀፅ 62 ላይ ለሥራ ወደ ውጭ አገር ለሚሄድ ማንኛውም ሠራተኛ አሰሪው የሕይወትና የአካል ጉዳት ካሳ የመድህን ሽፋን በአገር ውስጥ የመግባት ግዴታ እንዳለበት በመደንገጉ ለሥራ ወደ ውጪ አገር የሚሄዱ ዜጎች በስራ ላይ ሊደርስባቸው ለሚችል ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና አካላዊ ጉዳት እና ጥቃት ተገቢው ጥበቃ እንዲኖራቸው ለማድረግ ነው፡፡

በዚሁ መሰረት ለስራ ወደ ውጭ አገር ለሚሄድ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ሠራተኛ አሰሪው በአገር ውስጥ የሕይወትና የአካል ጉዳት ካሳ ኢንሹራንስ ለመግባት በሚያደርገው እንቅስቃሴ በመድህን ሥራ አዋጅ ቁጥር 746/2004 መሠረት ከብሔራዊ ባንክ ፍቃድ በማውጣት እየሰሩ የሚገኙ የኢንሹራንስ ድርጅቶች ግልጽነትና ፍትሃዊነትን በተከተለ አግባብ ተሳታፊ የሚሆኑበትን አሰራር ለመዘርጋት ይህ የአፈጻጸም መመሪያ እንዲወጣ ተደርጓል፡፡

## 2. አውጭው ባለሥልጣን

ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 923/2008 አንቀፅ 62(1) በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ለሥራ ወደ ውጭ አገር የሚሄዱ ዜጎች በአገር ውስጥ የሕይወትና የአካል ጉዳት ካሳ የመድን ሽፋን የሚያገኙበትን ሁኔታ ለመወሰን ይህንን የአፈፃጸም መመሪያ አውጥቷል፡፡

## 3. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "ለሥራ ወደ ውጭ አገር የሚሄዱ ዜጎችን የመድን ሽፋን ለመወሰን የወጣ መመሪያ 89/2013" □□□ □□□□ □□□□□□□

የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር
ሪከርድና ማህደር
Record and File
Ministry of Labour and Social Affairs

4. <u>ትርጓሜ</u>

በዚህ መመሪያ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

1. "**አዋጅ**" ማለት የኢትዮጵያ የውጭ አገር የሥራ ሥምሪት አዋጅ ቁጥር 923/2008 ማለት ነው፡፡
2. "**መድን**" ማለት አንድ መድን ሰጪ ከመድን ገቢው አረቦን በመቀበል በመድን ውል ውስጥ በግልፅ የተቀመጡና መድን ገቢው ለሚደርስበት ጉዳት ህጋዊ ኃላፊነትን ተከትሎ የካሳ ክፍያ ለመፈፀም የሚገባው ግዴታ ወይም በውለታው በግልጽ የተቀመጡ ሁኔታዎች የተከሰቱ እንደሆነ የተወሰነውን የካሳ ክፍያ ለመክፈል የሚያደርገው ስምምነት ነው፡፡
3. "**የመድን ሽፋን**" ማለት በውጭ ሀገር በስራ የሚሰማሩ ዜጎች የህይወትና የአካል ጉዳት ካሳ የመድን ሽፋን የሚያገኙበት ሁኔታ ማለት ነው፡፡
4. "**የመድን ፖሊሲ**" ማለት ማንኛውም መድን ሰጪ አረቦን ሲቀበል በመድን ውል የተጠቀሰው ሁኔታ የተሟላ እንደሆነ ለመድን ገቢው በውል የተወሰነውን ጥቅም ወይም ካሣ ለመክፈል የገባውን ግዴታ የሚያረጋግጥ ሰነድ ሲሆን የመድን ውል ምስክር ወረቀት፣ ክፍያ የተፈፀመበት ጊዜያዊ ሰነድ፣ የመድን ሽፋን ዕድሳት ደረሰኝ፣ የመድን ውሉን የሚያረጋግጥና ሌላ ሠነድ ይጨምራል፡፡
5. "**መድን ሰጪ**" ማለት የመድን ፖሊሲ የሚሰጥ ወይም የመድን ፖሊሲ ለመስጠትና የመድን ፖሊሲው የሚያስከትላቸውን ግዴታዎች ለመፈፀም ስምምነት የሚያደርግ ሰው ነው፡፡
6. "**የሕይወት መድን**" ማለት መድን ሰጪው አረቦን በመቀበል የመድን ገቢው በሞት ላይ ተመስርቶ በተፈፀመ ውል ለመድን ገቢው ወይም ለሌላ ተጠቃሚ አስቀድሞ የተወሰነ ገንዘብ ለመክፈል የሚገባው የመድን ውል ዓይነት ነው፡፡
7. "**አካል ጉዳት**" ማለት የመስራት ችሎታ መቀነስን ወይም ማጣትን በሚያስከትል ሁኔታ በስራ ላይ የሚደርስ ጉዳት ነው፡፡
8. "**ዘላቂ ከፊል የአካል ጉዳት**" ማለት ጉዳት የደረሰበትን ሠራተኛ የመስራት ችሎታ የሚቀንስ የማይድን በስራ ላይ የሚደርስ ጉዳት ነው፡፡



ሪከርድና ማህደር
Record and File
Ministry of Labour and Social Affairs

9. **"ዘላቂ ሙሉ የአካል ጉዳት"** ማለት ጉዳት የደረሰበት ሠራተኛ ማንኛውንም ደሞወዝ የሚያስገኝ ሥራ እንዳይሰራ የሚከለክለው የማይድን በስራ ላይ የሚደርስ ጉዳት ነው፡፡

10. **"የአስግድዶ መደፈር ጉዳት"** በውጭ አገር በስራ በተሰማራች ዜጋ ላይ በስራ ቦታዋ በአሰሪዋ ወይም በአሰሪዋ ቤተሰብ በኃይል በሚፈፀም የወሲብ ጥቃት የሚደርስ የአካልና የአዕምሮ ጉዳት ማለት ነው፡፡

11. **"ራስ ማጥፋት"** በውጭ አገር በስራ የተሰማራ ዜጋ በሚደርስበት ጫና ምክንያት ራሱን ሲያጠፋ ማለት ነው፡፡

12. "ሰው" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

13. በዚህ መመሪያ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ በአዋጁ ትርጉም የተሰጣቸው ቃላትና ሃረጎች ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

14. በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለፀው ድንጋጌ የሴት ፆታንም ይጨምራል፡፡

5. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ፡-

1. ለሥራ ወደ ውጭ አገር በሚሰማሩ ዜጎች፣
2. በአሠሪዎችና ኤጀንሲዎች እና
3. በመድን ሰጭ ድርጅቶች ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

6. <u>የመድን ሽፋን ለመስጠት ብቁ ስለመሆንና ስላለመሆን</u>

6.1. <u>የመድን ሽፋን ለመስጠት ብቁ ስለመሆን</u>

ወደ ውጭ አገር በስራ ለሚሰማሩ ዜጎች የመድን ሽፋን የሚሰጥ ድርጅት የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፡፡

ሀ. ከብሔራዊ ባንክ የመድን ሽፋን ለመስጠት የሚያስችል ፈቃድ፣

ለ. በብሔራዊ ባንክ የተረጋገጠ የመድን ፖሊሲ፣

ሐ. በአገሪቱ በሚገኙ ክልሎች ተደራሽ መሆኑን የሚያረጋግጥ መረጃ፣

መ. ከብር 50,000,000,000 /ሃምሳ ሚሊዮን ብር/ ያላነሰ የካፒታል መጠን እና በህጋዊ የውጭ ኦዲተር የተረጋገጠ ያለፈ አመት የሂሳብ ሪፖርት፣

ሠ. የታደሰ የዘመኑ የንግድ ፈቃድ፣

ረ. የመድን ሽፋን በመስጠት ስራ ላይ ቢያንስ የአሥር ዓመት ልምድ ያለው መሆን፡፡

## 6.2. የመድን ሽፋን ለመስጠት ብቁ ስላለመሆን

ከዚህ በታች የተመለከቱት ለስራ ወደ ውጭ አገር ለሚሄዱ ዜጎች የመድን ሽፋን ለመስጠት ብቁ አይሆኑም፡፡

ሀ. ወደ ውጪ አገር ዜጎችን በስራ ከሚያሰማሩ ኤጀንሲዎች ጋር በሽርክና የሚሰራ ወይም የአክሲዮን ድርሻ ያለው፣

ለ. በኤጀንሲው ስራ አስኪያጅነት እና በሠራተኛነት የጥቅም ግንኙነት እንዳለው በማስረጃ ከተረጋገጠ፣

ሐ. የሚኒስቴሩ፣ አግባብ ያለው ባለስልጣን፣ የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የኢምግሬሽንና ዜግነት ጉዳይ ዋና መምሪያ፣ የፖሊስ ኮሚሽን ወይም አዋጅ 923/2008 የሚያስፈጽም የመንግስት አካል ማንኛውም የሥራ ኃላፊ ሠራተኛ ወይም በውጭ አገር የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ አመራር አባል እና የእነዚህ ቤተሰቦች ከመድን ሽፋን ሰጪ ድርጅት ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ግንኙነትና ድርሻ ያላቸው መሆኑ በማስረጃ ከተረጋገጠ የመድን ሽፋን ለመስጠት ብቁ አይሆኑም፡፡

## 7. የመድን ሽፋን የሚሰጥባቸው ሁኔታዎች

1. በውጭ አገር በሥራ የተሠማራ ሠራተኛ የህይወት መድን ሽፋን የሚሠጠው፡-

ሀ. በተፈጥሮ፣ በድንገተኛ አደጋ ወይም ሥራ ላይ እያለ ራስን የማጥፋት አደጋ ሲያጋጥመው፣



የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር
ሪከርድና ማህደር
Record and File
Ministry of Labour and Social Affairs

ለ. ሠራተኛው በሄደበት አገር በተፈጥሮም ሆነ በድንገተኛ አደጋ የሞተ እንደሆነ ለቀብር ማስፈፀሚያ እና ለሠራተኛው ንብረት ማጓጓዣ ነው፡፡

2. በውጭ አገር ለሥራ የተሠማራ ሠራተኛ የአካል ጉዳት መድን ሽፋን የሚሠጠው በስራ ላይ እያለ፡-

ሀ. ዘላቂ የአካል ጉዳት ወይም ከፊል የአካል ጉዳት የደረሰበት ከሆነ፣

ለ. የአዕምሮ መታወክ ካጋጠመው፣

ሐ. የአስገድዶ መደፈር ጉዳት ከደረሰ፣ በተጨማሪም በዚህ ምክንያት ዘላቂ ጉዳት ወይም የአዕምሮ መታወክ ያጋጠመ ከሆነ የመድን ሽፋን ያገኛል፡፡

3. የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀፅ 1 እና 2 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የመድን ሽፋን አገልግሎት የሚሰጠው ድርጅት የሽፋኑን ዋስትና መጠን በግለሰብ እና በዕድሜ ለይቶ በዝርዝር ማቅረብ አለበት፡፡

## 8. <u>የመድን ሽፋን ፖሊሲ ሠነዶች</u>

በውጭ አገር በሥራ ለሚሠማራ ሠራተኛ የመድን ሽፋን በሚሰጠው የመድን ድርጅት፡-

1. የሚዘጋጁ የመድን ሽፋን ፖሊሲዎች፣ ሠርተፍኬቶች፣ የማመልከቻ ፎርሞች እና የዋስትና ሠነዶች በመድን ህጉ መሠረት እና በብሔራዊ ባንክ የፀደቁ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡
2. የሚቀርቡ ሠነዶች፣ ፖሊሲዎች፣ የምስክር ወረቀቶች፣ የውል ሠነዶች ተከታታይ ሲሪያል ቁጥር የያዙ መሆን አለባቸው፡፡

## 9. <u>የመድን ሽፋን የጊዜ ገደብ</u>

1. የመድን ሽፋን የጊዜ ገደብ በውጭ አገር በሥራ የሚሠማራ ሠራተኛ ከአሠሪው ጋር በገባው የሥራ ውል ዘመን መሠረት ይሆናል፡፡
2. የሠራተኛው የቅጥር ውል የሚራዘም ከሆነ የመድን ሽፋን ውሉ እንደሁኔታው መታደስ አለበት፡፡



የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር
ቃርድና ማህደር
Record and File
Ministry of Labour and Social Affairs

3. የሠራተኛው የቅጥር ውል ከመድን ፖሊሲው ጋር ተያይዞ መቅረብ ይኖርበታል::
4. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10/3 መሠረት የሚቀርብ የመድን ፖሊስ ተቀባይነት ሊኖረው የሚችለው በዚህ መመሪያ አንቀፅ 6 መሠረት ብቁ ከሆኑና ዝርዝራቸው በሚኒስቴሩ ከተመዘገበው የመድን ሰጪ ድርጅቶች ብቻ ነው::
5. የመድን ሽፋን ሰጪ ድርጅት በገባው ውል መሠረት በውጭ አገር በሥራ ለሚሰማሩ ዜጎች ተገቢውን የመድን ሽፋን የማይሰጥ መሆኑ ሲረጋገጥ የሚታገድና በህግ የሚጠየቅ ይሆናል::

## 10. የመድን ሽፋን ሰጭ ድርጅት በፖሊሲ ላይ ማካተት ያለባቸው ጉዳዮች

1. የሚሰጣቸውን የመድን ሽፋን አገልግሎቶች በግልፅና በዝርዝር በፖሊሲው ላይ ማስቀመጥ ይኖርበታል::
2. የመድን ሽፋን የሚሰጥበትን አገር ስም በፖሊሲው ላይ በግልፅ መጥቀስ ይኖርበታል::
3. የአረቦን ክፍያ መጠን በፖሊሲው ላይ በግልፅ ማስቀመጥ ይኖርበታል::
4. በመድን ሽፋን የሚጠየቀውን አረቦን የሚከፍለው አሠሪው ይሆናል::
5. በመድን ሽፋን የሚከፈል አረቦን ክፍያ በመድን ህጉ በተደነገገው መነሻነት ግልፅና ፍትሃዊ መሆን ይኖርበታል::
6. ድርጅቱ በሚሠጠው የመድን ሽፋን የሚከፈለው የካሳ ክፍያ ለሠራተኛው ወይም ለህጋዊ ወራሹ መሆኑን በፖሊሲው ላይ በግልፅ መጥቀስ ይኖርበታል::
7. ሠራተኛው የሥራ ውሉን አቋርጦ ወደ አገሩ ቢመለስ አሠሪው የከፈለው የአረቦን ክፍያ ሠራተኛው ለሥራ የቆየበት ጊዜ ታሳቢ ተደርጎ ተመላሽ ሊደረግ ይችላል::

Record and File
Ministry of Labour and Social Affairs

## 11. የመድን ሽፋን

በውጭ አገር በሥራ ለሚሠማራ ሠራተኛ የሚደረግ የመድን ሽፋን በፆታ፣ በዕድሜ፣ በተመደበበት የስራ ሁኔታ ልዩነት መደረግ የለበትም፡፡

## 12. ለካሣ ክፍያ ጥያቄ የሚያስፈልጉ የሠነድ ማስረጃዎች

1. ሠራተኛው ለደረሰበት አደጋ የካሣ ጥያቄ ሲቀርብ መሟላት ያለባቸው ማስረጃዎች፡-
   - ሀ. በተፈጥሮ እና በድንገተኛ አደጋ ለስራ ከተሠማራበት አገር ሕይወቱ ማለፉን የሚያረጋግጥ የህክምና ማስረጃ ምስክር ወረቀት፣
   - ለ. ዘላቂ ወይም ከፊል የአካል ጉዳት ደርሶበት ከሆነ የጉዳቱን ዓይነትና መጠን የሚያረጋግጥ የህክምና ማስረጃ ምስክር ወረቀት፣
   - ሐ. የአእምሮ መታወክ ካጋጠመው የህክምና ማስረጃ ምስክር ወረቀት፣
   - መ. የአስገድዶ መደፈር ድርጊት በሠራተኛው ላይ የተፈፀመ ከሆነ የጉዳቱን ዓይነትና መጠን የሚያረጋግጥ የህክምና ማስረጃ ምስክር ወረቀት መቅረብ ይኖርበታል፡፡
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1(ሀ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ሠራተኛው በተፈጥሮ ወይም በድንገተኛ አደጋ ሞት ሲያጋጥመው ህጋዊው ወራሽ የካሣ ጥያቄ ለማቅረብ የሚከተሉትን ማሟላት ይጠበቅበታል፡፡
   - ሀ. ወራሽ ስለመሆኑ በፍርድ ቤት የተረጋገጠ የወራሽነት ማስረጃ፣
   - ለ. ያገባ ከሆነ የጋብቻ ምስክር ወረቀት፣
   - ሐ. ልጆች ካሉና ለአቅመ አዳም ካልደረሱ በፍርድ ቤት ሞግዚት እንዲሆን የተወሰነበትን ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

## 13. የካሣ ክፍያ መጠን

1. የህይወት ካሣ መነሻ ክፍያ መጠን እንደሚከተለው ይሆናል፡፡
   - ሀ. ሠራተኛው ለስራ በተሰማራበት አገር በተፈጥሮ ሕመም ከዚህ አለም በሞት ሲለይ ለህጋዊ ወራሾቹ ብር 300,000 የካሣ ክፍያ ይከፈለዋል፡፡

ሪኮርድና ማህደር
Record and File
Ministry of Labour and Social Affairs

ለ. ሠራተኛው በስራ በተሰማራበት አገር ስራ ላይ እያለ በድንገተኛ ሞት፣ በአደጋ ሞት ወይም በራስ የማጥፋት ሞት ከዚህ ዓለም ሲለይ ለህጋዊ ወራሽ ብር 350,000 የካሣ ክፍያ ይከፈለዋል፡፡

2. ዘላቂ የአካል ጉዳት፣ ከፊል የአካል ጉዳት፣ የአእምሮ መታወክ እና በአሠሪው አስገድዶ የመደፈር ጉዳት የደረሰበት ሠራተኛ የካሣ ክፍያ መጠን የህክምና ማስረጃ በሚያረጋግጠው መሠረት ይከፈላል፡፡

3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 2 በሚደርሰው የአካል ጉዳት መጠን የሚከፈለው ክፍያ የመድን ሽፋን ሰጪ ድርጅት በሚያቀርበው ፖሊሲ ላይ በዝርዝር መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

14. **የካሣ ክፍያ ጥያቄ የሚቀርብበት ቦታ**

የመድን ሽፋን በተሰጠው ሠራተኛ ላይ ለሚደርስ ጉዳት የሚጠየቀው የካሣ ክፍያ የሚቀርበው በመድን ድርጅቱ ዋና መ/ቤት ወይም ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ይሆናል፡፡

15. **የካሣ ክፍያ አፈፃፀም**

1. በተገባለት የመድን ሽፋን መሠረት ጉዳት ለደረሰበት ሠራተኛ ወይም ለህጋዊ ወራሽ ክፍያ እንዲፈፀም በአሠሪውና በኤጀንሲው ማስረጃዎች ተሟልተው ለመድን ሽፋን ሰጪ ድርጅት የክፍያ ጥያቄ መቅረብ አለበት፡፡
2. የመድን ሽፋን ሰጪ ድርጅት በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀፅ 1 በተደነገገው መሠረት ማስረጃዎች ተሟልተው እንደቀረቡ በ10 ቀናት ውስጥ የካሣ ክፍያውን መፈጸም ይኖርበታል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 በተደነገገው መሠረት መድን ሽፋን ሰጪ ድርጅት ክፍያውን ካልፈጸመ ራሱ ድርጅቱና አሠሪው በሕግ ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡
4. የመድን ፖሊሲ ተቀባይነት ሊኖረው የሚችለው በዚህ መመሪያ አንቀፅ 6 መሠረት ብቁ ከሆኑ መድን ሰጪ ድርጅቶች ሲቀርብ ብቻ ነው፡፡

መዝገብና ማህደር
Record and File
Ministry of Labour and Social Affairs

## 16. ስለመድን ሽፋኑ አፈፃፀም ሪፖርት አቀራረብ

ለክትትልና ድጋፍ ያመች ዘንድ የመድን ሽፋን የሰጠው ድርጅት፡-

1. የተከፈለ አረቦን ክፍያ ዝርዝሮችን፣
2. የቀረቡ የካሣ ክፍያ ጥያቄዎችን፣
3. የካሣ ክፍያ ቀርቦባቸው ያልተፈፀሙ ክፍያዎችን፣
4. ሌሎች ከመድን ሽፋን ጋር የተያያዙ ስታትስቲካል መረጃዎችን የአፈፃፀም ሪፖርት በየስድስት ወሩ ለሚኒስቴሩ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
5. የመድን ሽፋን ሰጪ ድርጅቱ አፈፃጸም ሚኒስቴሩና የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በተገኙበት በየስድስት ወሩ በጋራ ይገመገማል፡፡

## 17. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው፣ ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

## 18. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ የአፈፃፀም መመሪያ ከ መስከረም 8 ቀን 2011 ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ፊርማ ____________________

ሂሩት ወ/ማርያም ቶክቶል (ዶ/ር)
ሚኒስትር



አዲስ አበባ